# "ግንባርህን አሳያቸው "

## በፀጋዬ ገብረመድህን ( ደብተራው ) ቋራ 1977 ዓ.ም.

ግርማ ሌሊት ድምፀ አራዊት ቅጥቃጤና ቅዠት
ሲያማስን ሲያባባን ረዝሞብነ ውድቅት
ሌሊቱ ሲዋገድ አጥቢያ ኮከብ ሲቀድ
ታጥቀን ብንነሳ ነግቶልናል ብለን
ተፍ ብለው ተነስተው ውህዳጣን ውህዳን
አዛዥ ናዛዥ ሁነው ሙሉ ባለ ስልጣን
እናንት መች ነቃችሁ እኛ ነን የነቃን
እነግራችኋለን እናንተ ስትነቁ
መንቃታችሁ አይቀር በትግስት ጠብቁ
ብለው ሰደዱነ ወደ ምኝታችን፣ ወደ ቅጥቃጤአችን፣ ወደ ቅዠታችን።

አድማሱን ፈልቅቃ ፀሐይ ብቅ ብላ ጨራ ስትፈነጥቅ
ሳይደርሰነ ቀረ ምናምን ነፀብራቅ
ትወርዳለች አሉን ገነት ተመሬት
ልታድለን ትፍሲት ልትሰጠን ሐሴት
ሰላም ልትነግስ ሊያከትም ጦርነት
በወርቅ በእንቁ ልን-ነድ ልንመስል ማህቶት
ከምዝበራ ጋራ ልንሰናበት
ላንዴም ለሁሌውም ልንወጣ አርነት።

ይህነን ምስራች እያወሱልነ
ሲነጋ ሲጠባ በጣመ አንደበት
ጆሮአችን ደለበ ሰባ እንደ ሙክት።

በገነቷ ፈንታ ለካስ ሲኦል ወርዳ
ግምኛ ጠበቅነ አበዛነ ፍዳ
የፋሽሽቶች ተስፋ የተንቀጠቀጠ በዲስኩር ምንሜና
እያደር የሚርቅ እንደ ሰማይ መና
እንኳንስ አካላት ተራበ ህሊና
ወግ ማዕረግ አውልቆ ለበሰ ገበና።

ነፃነት ሐርነት ተፈጥረው ባንድ ላይ
ዝናቸው ማራኪ ስማቸው ሰው ገዳይ
ለነሱ ያደረ ምንኛ ማሰነ
ተመጽደቁ በፊት እየተኮነነ
ተኮንኖ መጽደቅ ሙቶ ህይወት መንሳት ጠውልጎ መለምለም
የተፈጥሮ ስርዓት የሚኖር ዘላለም።

መታፈን፣ መረሸን፣ መዘልዘል፣ መገደል፣ መጠበስ፣ መታመስ
መቀጥቀጥ፣ መረገጥ፣ መሰደድ፣ መዋረድ፣ መታሰር፣ መመተር፣ የመከራ ጡማር
የመከራ ጠማር የጥፋት ሰንክሳር
ሲነበብ፣ ሲነበብ ሲንት ዓመት አለፈ
ተእንግዲህስ ይብቃ ታምር ሊነበብ ነው በቀይ የተጣፈ
ባርነት ግዙነት ነፃነትን ማርከው በለሱ ቀንቷቸው
ካባዋን አጥልቀው ኩታዋን ደርበው
ጫማዋን ተጫምተው ውበው ተኳኩለው
በዓርነት አምሳል በነፃነት አምሳል ተናገሩ ደፍረው
ከቶ  አንስታትም የኛን ነፃነት
ለዛዋ ላህይዋ አለው ምልክት
ሰላምን የሚያወርድ የሚያቀል ምሕረት።

አጀብ ! አጀብ ! ዲሞክራሲ
ከመስኮብ የመጣች ፈላሲ
ሃሳዊ መሲህ የቀትር ከይሲ
ግና ኮ፣ ግና ኮ የመረጡልነን ደግመን ተመረጥነ
የሰየሙልነን ደግመን ተሰየምነ
ያሰቡልነንም እሽ በጎ ታልነ
ነፃነት ታጣ እንጅ መብትማ  ሞልቶነ
ዘመናይ መሳፍንት ዘመናይ መኳንንት እናንተ ጌቶቹ
ተእንግዲህ ኤይመችም ለናንተ ታች ታቹ
መጡብነ ብለን እንግዲህ አንናገር ካፋችን አይወጣ
የናንት ምጣት በዝቷል እኛ ነን ምንመጣ
ብድር መች ይቀራል እንወረድ ጣጣ።

አልገባነ ብኋል ከቶ አልተሰባንም የናንተ ይትባሃል የናንተ አማርኛ
ብንጮህ ብንታክት አልተማርንም እኛ
ሰላምታ ለመስጠት እጅ ዘርጉ አላችሁን እጅ ስጡ አላችሁን
እጅ ሰቶ ሰልም ታባት ያልቆየንን
እንዳንጎነበስ ዝናራችን ያዘን
ዝናር እንዳንፈታ ሰብቁ ጠበቀብን።

ፀሃዩን ጋበኑን ተወጡት አላችሁ እንድንደርስ ተግብ
እራሳችን ጣይ አይችል የሚአንገበግብ
እናንተስ ይዛችሁ ባለቆብ ጭንቅላት የማያሳስብ
ምንኛ ይገርማል ያበጇልን ስርአት
እነ ጓድ ግራዚያኒ ሁነውነ ሞግዚት
የህሊና ሞቅህ የአይምሮ እስር ቤት
የመብት የነፃነት ማሰሪያ ሰንሰለት
ምንኛ ስርዓት ምንኛ መንግስት መሰረቱ ጦርነት
መቃን ጉበኑ ሞት እልቂት
ጣራ ግድግዳው ረሀብ መቅሰፍት
መዋቅር የሚሉ ጉግ ማንጉግ
ከአናት ሰፍሮ እንደ መርግ፣ ወኔ መጣጭ እንደ ሰፍነግ
ባንዳ አጥር ሆኖ ሲያረገርግ፣ መከታ ጠፍቶ ከለላ ጥግ
እንባ ሲዝቀዝቅ እንደ አፍላግ
የህፃት የአሩግ።

መደየን እንጅ መኮነን፣ እንደ ኩንቲ እንደ ጋኔን
መዋቅር፣ መዋቅር፣ መዋቅር፣ የትም የትም መዋቅር
በየብስ፣ ባየር፣ በባህር።

ሃሳብ ሲንተከተክ ተከድኖ ባርምሞ
ሕሊና ላይማትር ምሎ ተፈጥሞ
ልብን ሲያሽልበው ያለውል ታግሞ
ቆሽት ድብን ሲል ተራሞ፣ ተራሞ
የህይወት ምልክት የነብስ ጠብታ ተወግዶ አክትሞ
ምንኛ ተከበከብነ ምንኛ ተኮላመጥነ አያ
ለጆሮአችን ዘብ ቁሞልን ለአፋችን ዋርድያ
በየቦታው ሰንተርያ አወይ አንዷት ምዕራፍ መሰናዘሪያ።

ምድር  ምህዋሯን ለውጣ ውደቷን አስረዝማ
አመት  ሲ ለ ጠ ጥ እንደ ጎማ
ሌት ተቀን ፀብ አብቅለው
በአልመሸ አልነጋ ተጣልተው
የሚገለግል ጠፍቶ ዳኛ
አገር ሆኖ ህመምተኛ
አባዜ ይዞት መጋኛ
ከመስኮብ የመጣ ቁራኛ።

አዚም ጥሎብን እፅ አደንዛዥ
በስጋችን አዛዥ
በነፍሳችን አዛዥ
በእጅ እግራችን አዛዥ
በአይምሮአችን አዛዥ
ባሳባችን አዛዥ
በቤታችን አዛዥ
በንብረት ሁሉ አዛዥ
በልጃችን አዛዥ።

ዴሞክራሲ ቀስላ ተጨማልቃ በዕዥ
ፍትህ ርትህ ተጠራምቃ ስትል ጥርዥ ብርዥ
ዋየ ወዮ የኢትዮጵያ ሕዝብ
የአርበኝነት ድርሳን የጀግንነት መዝገብ
ተስተጋብተህ ባትነበብ ዘበቱብህ አህዛብ።
አርሶ አደሩ ታልቦ ላብአደር ተጨምቆ
ሃውልቶች ተተክለው ተሩቅ የሚጣሩ
ህንፃዎች ተሰርተው ከፀረ አረያም የሚፈካከሩ
ከምፃት በኋላ በአጸደ ነፍስ ሆኖ አለም የሚያይባት ምዝብር ሰርቶ አደሩ
የናንተ ነው አሉን ምርቱ ፍሬ ምድሩ
ባለጸግ ሁነው እነሱ በኮሩ
የናንተ ነው አሉን ሞገስና ክብሩ
እነሱ ባጌጡ እነሱ ባማሩ
የናንተ ነው አሉን ክብርና ሞገሱ
እንደ ሰሚ ታቦት ሁሌ ሲወደሱ።

መንጋ ፋሽሽት ዱለቻ
ቃላቸው አንድ ስጡ ብቻ
ቋንቋቸው አንድ አምጡ ብቻ
አስቀድመው ቁጣ ዛቻ
አርቲ ቡርቲ ለጌቻ
አምጡ አምጡ አምጡ አምጡ
ነጋ ጠባ ተቦጥቦጡ
ሰማይ ውጡ ምድር ፍረጡ
ሃገር መሬቷን ቧጡ
ብቻ ብሪቱን አምጡ
እህህ ብላችሁ አምጡ።

ብራችንን ሰጠነ
ጉልበታችንን ከሰከስነ
ወረት ጥሪት አሟጠጥነ
ይብስ አታምጣ እያልነ
ሃገር የኛ መስሎነ
ታገር ያደርን መስሎነ
ልጅ እናሳድግ ብለነ
ክብራችንን ሰተን ሀፍረት ተቀበልነ
ወግ ታሪካችንን በርካሽ ለወጥነ።

አሜን አሜን ብለን ስንከፍልለት ጊዜ የተባለ ግብር
ይጠይቀን ገባ በብር ላይ በጎር
ልጅ ከገበርንማ ምን ቀረን ለሃገር
ቀልዱ በዛ ፌዙ በዛ አደረጉን አሻንጉሊ
ኢትዮጵያን እያጣናት ዓለም አሉን የናንተ ናት የሰርቶ አደሩ ናት
አገርማ ጠፍታ በዚያ ሰሞን ስንባክን ስንካለብ
ታይቷል አሉ ዱካዋ ወደ ኩባ ወደ መስኮብ
ንሳ ጎበዝ ፍለጋ ነቅንቅ ዘገር
አገር ጠፍታ እንሬት ትቀር።

በአንድነት ተነስተን ታልወጣን አሰሳ
አገር አትገኝም ብንፈርጥ ብንነሳ
ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስ፣ አረ ተነስ
ቤትህ ሲተኮስ አገር ሲጤስ
ያባት ታሪክ ዳዋ ሳይለብስ
ደብዛው ሳይጠፋ ሳይረምስ
ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስ።

እሸን ተዋት እዛው ትንደድ
ከፋሽሽት ጋር ትሞዳሞድ
እንቢኝ ናት ያንተ ዘመድ
የጀግና ክፍል የጎበዝ ገድ
የፋኖ ጌጥ የታጋይ ዘውድ
እምቢኝ ናት ያንተ ዘመድ
እሷን ይዘህ በሻህ ውጣ በሻህ ውረድ
በትግል ፍኖት በገድል መንገድ።

የሰላቶ ልጅ ሰላቶ የፋሽሽት ግራዚያኒ
ተእንግዲህስ በቃኝ ላማ ሰበቅታኒ
መደየን ተራህ ነው እንደአባትህ ማኒ
ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስ
ቤትህ ሲተኮስ አገር ሲጤስ።

አገር ስትሆን ማሰሮ
ሰው ሲቀቀል እንደ ንፍሮ
ጎርናባቸው አልቀመስ በላቸው
ፍልጠት ቁርጠት ሁንባቸው።

ያንበሳ ልጅ የኩረምቱ
ሲገርም እንጅ ደግነቱ፣
ሲጣላማ ሲነኩቱ
እልፈት ዓለም ምፃቱ
ድብልቅልቅ ሲል መሬቱ
ወኔና ፍርሀት ሲሟገቱ
መምረጥ ሲመጣ ተሁለቱ
የጀግና ልጅ የጥዋቱ
አገዳ የሚለይ እንደ አባቱ
የፋሽሽት አብነቱ
የባንዳ አድር ባይ መቅሰፍቱ
የማይታጠፍ እምነቱ
ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስ
በፋስሽት አለንጋ አትጠበስ።

ይጠራሃል ደኑ ይጠቅስሃል ዱሩ
ከመሸገበቱ ያባትህ ጀግንነት ኩራትና ክብሩ
ሙታንታውን ተወው ቁምጣው መቸ በጀህ
ሱሪህ ነው ታሪክህ ሞገስ የሚሰጥህ
ፀጉርህን ንቀሰው አየሩን ይዳሰው
አሟጨው ጥርስህን ፀዳሉን ያፍልቀው።
ይመርብህ ላንዴ እስኪ ታጠቅ ልይህ አካል ገብናናየ
ምድሪቱን አውዳት አደሴ ሽቶየ
እስኪ እነየው ከልካይህን በናትህ ጎራ ባባትህ ቀየ
አያመሻሹበትም አያድሩበት ቦታ
የፋሽስት እንግዳ መች አለው ይሉንታ
ስጋችንን ኮመኮመ፣ያማረውን አጣጣመ

ምንቀረ ጨገሬታ
ቤቱን ይሂድ እንጅ ምንድር ነው ዝመወታ
ጥይትህ ላካት ትሁነው ሸኝታ
ታድርሰው ተመስኮብ ተዳር ተደፋታ።

የኛማ ባላንጦች ተገሳፅ አይገባቸው
ቡጢ ክርናችንም መቸ ጠቀማቸው
ግ ን ባ ር ነው የሚፈሩት ብርክ የሚያስዝአቸው
ግንባረህን አሳያቸው
ምግባርህን አስተምራቸው።

አይታክቱ ፋሽሽቶች ታሪክ ይመርምሩ
የቆየ የቅድም ያገሬ ልቦና ለፋሽሽት ሲሰግድ፣ለባንዳ ሲሳለም
አልታይቶም፣ አልተሰምቶም፣ አልተጥፎም

ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስ
ቤትህ ሲተኮስ አገር ሲጠስ
ያባት ታሪክ ዳዋ ሳይለብስ
ደብዛው ሳይጠፋ ሳይረምስ
ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስ፣ ተነስስስስስስስስስስ።